እምሃይማኖቶሙ ፡ በዘኮነ ፡ ከዊኖ ፡ እመዓርግ ፡ ለይረዱ ፡ እምኔሃ ፡ ኅበ ፡ ዘይቴሐት ።

፩ሺ፮፻፶ ምዕራፍ ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ፍትሐ ፡ ዘነኔ ፡ በበይነ ፡ ዘይወስድ ፡ ኅበ ፡ አምልኮ ፡ ካልእ ፡ ዘኢኮነ ፡ አምላከ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ልዑል ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘከመ ፡ ረቃዪ ፡ ወመሠርይ ፡ ወተጠይሮ ፡ በአንጽፎ ፡ ሐመድ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወሐመር ፡ ወበቀልት ፡ ወሕጠታተ ፡ ዛጉል ፡ ወፋል ።

፩ሺ፮፻፶፩ ትቤ ፡ ወለመሠርይ ፡ ኢታሕይዎ ። መጽ ፡ ብእሲኒ ፡ ወብእሲትኒ ፡ እመቦ ፡ ዘኮኑ ፡ ሐራስያነ ፡ አው ፡ ዘሥራይ ፡ ሞተ ፡ ለይሙቱ ፡ ወበእብን ፡ ለይውግርዎሙ ፡ እስመ ፡ ጊጉያን ፡ እሙንቱ ፡ ወደሞሙ ፡ዲበ ፡ ርእሶሙ ።

፩ሺ፮፻፶፪ ትሔ ፡ ወኢይትረከብ ፡ በውስቴትክሙ ፡ ዘየኅሥሥ ፡ ትምህርተ ፡ ሐረሳውያን ፡ ወማእምራን ፡ ወኢ ፡ ዘያደሉ ፡ ለገጽ ፡ ወኢ ፡ መሠርይ ፡ ወኢ ፡ ዘይጤየር ፡ ወኢ ፡ ዘይረቂ ፡ ርቅየተ ፡ ወኢዘይሴአሎሙ ፡ ለሰብአ ፡ ሐሪስ ፡ ወኢ ፡ ለመንቅሕያነ ፡ ምዉት ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ በቅድመ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ።

፩ሺ፮፻፶፫ ረስጣ ፡ ፳ወ፬ቱ ፡ ረስጣ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ መሠርይ ፡ ወዘይጤየር ፡ ዲበ ፡ አንጽፎ ፡ ሐመድ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወሕጠታተ ፡ ዛጉል ፡ ወመንቅሕያነ ፡ ምዉት ፡ ወመፈክራነ ፡ አሕላም ፡ ወሰብአ ፡ ፋል ፡ ወገባርያነ ፡ ኵርበታት ፡ ይኅድጉ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይሰደዱ ።

፩ሺ፮፻፶፬ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ወኢይሳተፍ ፡ ፩ዱ ፡ እመሃይምናን ፡ ምስለ ፡ መሠርያን ፡ ወማእምራን ፡ ወዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ወተሳተፎሙ ፡ ወዘይሴአሎሙ ፡ ወያጸድቅ ፡ ቃሎሙ ፡ ወዘሂ ፡ ያበውአሙ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወቦአ ፡ ቤቶሙ ፡ ወበልዐ ፡ እክሎሙ ፡ ወሰትየ ፡ ስቴሆሙ ፡ እመሂ ፡ ኮነ ፡ እምካህናት ፡ ለይደቅ ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወይክልእዎ ፡ እምትድምርተ ፡ መሃይምናን ፡ ወእመሂ ፡ ኮነ ፡ እምሕዝባውያን ፡ ይትገኀሥ ፡ እምተደምሮቶሙ ፡ ወለእመ ፡ ነስሐ ፡ የሀብዎሙ ፡ ንስሐ ።



ኖታቸው ፡ የተመለሱ ፡ ሰዎች ፡ ከመዓርጋቸው፡ ወደ ፡ ዝቅተኛ ፡ መዓርግ ፡ ይውረዱ ።

፩ሺ፮፻፶ ፫ኛ ፡ ምዕራፍ ። ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ እንደ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ አልሆነ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ ስለሚወስድ ፡ ስለቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ እንደሚረጭ ፡ ሥራይ ፡ እንደሚያደርግ ፡ አመድ ፡ በመነስነስ ፡ በእንጨት ፡ ፍሬ ፡ በተረር ፡ ቃሞ ፡ በሰሌን ፡ በዛጎል ፡ ቅንጣት ፡ በጥንቆላ ፡ እንደማሚረት ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ፮፻፶፩ ትቤ ። መሠርይን ፡ አታድነው ። (ዘጸ ፡ ፳፪ ፡ ፲፰) ። መጽ ። ወንድና ፡ ሴትም ፡ ሟርተኞች ፡ ወይም ፡ መሠርዮች ፡ ቢሆኑ ፡ ሞትን ፡ ይሙቱ ። በደንጋይም ፡ ይውገሩአቸው ። በደለኞች ፡ ናቸውና ። ደማቸውም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ነው ።

፩ሺ፮፻፶፪ ትሂ ። የሟርተኞችንና ፡ የጠንቋዮችን ፡ ትምህርት ፡ የሚሻ ፡ ወይም ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የሚያደላ ፡ ወይም ፡ መሠርይ ፡ ወይም ፡ የሚያሟርት፡ ወይም ፡ መርጨትን ፡ የሚረጭ ፡ ወይም ፡ የሟርት ፡ ሰዎችንና ፡ ሙት ፡ አንሸዎችን ፡ የሚጠይቃቸው ፡ በውስጣችሁ ፡ አይገኝ ። ይህን ፡ ሥራ፡ የሚሠራ ፡ ሁሉ ፡ በፈጣሪያችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርኩስ ፡ ነውና ። (ዘዳ ፡ ፲፰ ፡ ፱-፲፪)።

፩ሺ፮፻፶፫ ረስጣ ፡ ፳፬ ። ረስጣ ፡ ፳፫ ። ሥር ፡ የሚምስ ፡ አመድ ፡ የእንጨት ፡ ፍሬ ፡ የዛጎል ፡ ቅንጣትም፡ በመበተን ፡ የሚያሟርት ፡ ሙት ፡ የሚያስነሠም ፡ ሕልም ፡ ተርጓሚዎችም ፡ የጥንቈላ ፡ ሰዎች ፡ ክታብ ፡ አድራጊዎችም ፡ ይተዉ ። ባይተዉ ፡ ይሰደዱ ።

፩ሺ፮፻፶፬ ኒቅያ ፡ ፳፪ ። ከምእመናን ፡ አንዱ ፡ ከመሠርያንና ፡ ከጠንቋዮች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አይሁን ። ይህንም ፡ ያደረገ ፡ የተቀላቀላቸው ፡ የሚጠይቃቸው ፡ ቃላቸውንም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ወደቤቱም ፡ የሚያስገባቸው ፡ ወደቤታቸውም፡ የገባ ፡ እህላቸውን ፡ የበላ ፡ መጠጣቸውንም ፡ የጠጣ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ከምእመናንም ፡ አንድነት ፡ ይከልክሉት ። ከሕዝባውያን ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከአንድነታቸው ፡ ይራቅ ። ቢመለሱም ፡ ንስሐ ፡ ይስጧቸው ።

